HUMAN RIGHTS WATCH

# “ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ”

## ለኦሮሞ ተቃውሞ መልስ ግድያና ዕስራት በኢትዮጵያ

# ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ የመንግስት የፀጥታ ሃይሎች እ.ኤ.አ. ከህዳር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በመላ ኦሮሚያ ክልል ተስፋፍቶ በነበረውን ህዝባዊ ተቃውሞ ተሳታፊዎች ላይ ከመጠን ያለፈ እና እስከ መግደል የሚያደርስ ሃይል ተጠቅመዋል፡፡ የኦሮሚያ ክልል በሃገሪቱ ከሚገኙ ክልሎች በስፋት ትልቁ ነው፡፡ 400 የሚገመቱ ሰዎች ተገድለዋል፤ በሺህዎች የሚቆጠሩ ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ ታስረዋል፤ እንዲሁም በመቶዎች የሚቆጠሩ እና ምናልባትም ከዚህ ቁጥር የሚልቁ ሰዎች ደግሞ ተገደው የተወሰዱበት ኣልተወቀም።

ተቃውሞው የጀመረው እ.ኤ.አ. በወርሐ ሕዳር 2015 ዓ.ም ሲሆን ዙሪያው በኦሮሚያ ክልል በተከበበው የኢትዮጵያ ዋና ከተማ- አዲስ አበባ በስተደቡብ ምእራብ 80 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው አነስተኛ ከተማ ጊንጪ ነው፡፡ የኦሮሚያ ክልል በኢትዮጵያ በርካታ ህዝብ የሚኖርበት ሲሆን 35 ሚሊየን የሚገመት የኦሮሞ ብሔር ይኖርበታል፡፡ የመንግስት ባለስልጣናት በጊንጪ የሚገኝ አንድ ጫካን (ደን) እና የእግር ኳስ ሜዳን ለኢንቨስትመንት ልማት የማጽዳት መወሰናቸውን ተከትሎ የተነሳው ተቃውሞ ቢያንስ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ በ17ቱንም ዞኖች ውስጥ ባሉ የተለያዩ 400 አካባቢዎች ተቃውሞው እንዲዛመት መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

እንደ አይን እማኞች መረጃ የጸጥታ ሃይሎች ሰላማዊ ተቃውሞ ለማድረግ ወደ ተሰበሰቡ ሰዎች በቀጥታ የተኮሱ ሲሆን በተመሰሳሳይ መንገድም ከፍተኛ ከበባ በማድረግ ሰዎችን ገድለዋል፣ እንዲሁም የማሰቃየት እርምጃ እና እገታ ፈጽመዋል፡፡ በኦሮሚያ የሚገኙ የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተቃውሞውን በመጀመርያዎቹ ወቅት ስለተቀላቀሉ ለእስር ከተዳረጉት እና ከተገደሉት በርካታዎቹ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች ናቸው፡፡ የፌዴራል ፖሊስን እና ወታደሩን የሚያካትተው የጸጥታ ሃይል ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ ሙዚቀኞችን፣ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን፣ የጤና ባለሙያዎችን፣ እና ከፖሊስ ጥቃት ሲያመልጡ ለነበሩ ተማሪዎች እርዳታ እና መጠለያ የሰጡ ሰዎችን በዘፈቀደ አስሯል፡፡ ምንም እንኳ በርካታዎቹ የተፈቱ ቢሆንም ቁጥራቸው በውል ማይታወቁ ሰዎች ክስ ሳይመሰረትባቸው የህግ ድጋፍ አገልግሎትም ሆነ የቤተሰብ ጉብኝት ተነፍገው በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ ሪፖርት የተጠናቀረው ከ125 በላይ ከሆኑ የአይን እማኞች፣ ተጠቂዎች፣ እና የመንግስት ባለስልጣናት ጋር በተደረገ ቃለምልልስ ነው፡፡ እ.ኤ.አ. ከ2015 ዓ.ም. መጨረሻ እስከ እ.ኤ.አ. ግንቦት 2016 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ የኦሮሞ ሰልፈኞች ላይ የተፈጸመውን እጅግ በጣም ከባባድ የሰብዓዊ ሙብት ጥሰት ክስተቶችን መዝግቧል፡፡

እ.ኤ.አ. በሕዳር ወር 2015 ዓ.ም. ተቃውሞው ሲጀመር ተቃዋሚዎች የፌዴራል መንግስቱን የልማት እቅድ በተመለከተ በተለይ ደግሞ የአዲስ አበባ የተቀናጀ ልማት ማስተር ፕላን (ማስተር ፕላኑ) በተሰኘው የዋና ከተማዋን የማዘጋጃ ቤት ድንበር ወደ ኦሮሚያ ክልል ድንበር ለማስፋፋት በነበረው እቅድ ላይ ያላቸው ቅሬታ ላይ አተኩረው ነበር፡፡ ተቃውሞ አድራጊዎቹ ማስተር ፕላኑ የኦሮሞ ገበሬዎችን እንደገና ሊያፈናቅል ይችላል የሚል ስጋት አላቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ገበሬዎች ላለፈው አስር አመት ያህል በተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች ሳቢያ ተፈናቅለዋል፡፡ እንደዚህ አይነት የልማት እቅዶች የበላዮቹን ጥቂት ግለሰቦችን ብቻ የጠቀሙ ሲሆን በአካባቢው ገበሬዎች እና ማህበረሰቦች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል፡፡

ሲቀጥል ተቃውሞው ባለመቆሙ መንግስት ለጉዳዩ ያልተለመደ ትኩረት በመስጠት እ.ኤ.አ. ጥር ወር 2016 ዓ.ም. ኢጋማሽ ላይ የማስተር ፐለኑን መሰረዝ አስታወቀ፡፡ ሆኖም በወቅቱ እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው ግድያ እና በገፍ የማሰር እርምጃዎችን ጨምሮ መንግስት በወሰደው የጭካኔ ርምጃ ምክንያት የተቃውሞ አድራጊዎቹ ቁጣ ሰፍቷል፡፡ ገበሬዎች እና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ተቃውሞ በማድረግ ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን የተቀላቀሏቸው ሲሆን የተቃውሞው ጥያቄም በመስፋት ብዙሃኑ የኦሮሞ ማህበረሰብ አባላት የሚጋሩትን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና የባህል በደሎችን ያካተተ ሆኗል፡፡

የሂውማን ራይትስ ወች ጥናት እንደሚያመለክተው እ.አ.አ. ከህዳር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ የተደረጉ እስከ 500 የሚደርሱ የተለያዩ የተቃውሞ ሰልፎችን ለመበተን የጸጥታ ሃይሎች ቀጥታ ወደ ሰዎች መተኮስን ጨምሮ እስከ መግደል የሚያደርስ ሃይል

ተጠቅመዋል፡፡ ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው ውስጥ እጅግ በጣም በርካቶቹ እንደገለጹት ፖሊስ እና ወታደሮች ያለበቂ ማስጠንቀቂያ ወይንም ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ ሰልፈኞች ላይ በቀጥታ ተኩስ ከፍተዋል። ውሃ እና የጎማ ጥይትን ጨምሮ የመግደል ደረጃ የማያደርስ ምንም አይነት የተቃውሞ ሰልፈኞችን መቆጣጠሪያ መንገድ አልተጠቀሙም፡፡

ተቃዉሞ ሰልፎች በተደረጉበት ግዜ ሁሉ የመንግስት ጸጥታ ሃይሎች በደርዘኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ እስር ቤት አጉርዋል፤ እንዲሁም በበርካታ አካባቢዎች ቤት ለቤት ፍተሻ በማድረግ ተማሪዎችን አስረዋል፡፡ ተማሪዎቹን በቤታቸው ውስጥ ለመደበቅ የሞከሩትንም ይዘዋል፡፡ የፀጥታ ሃይሎች በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ ተደማጭነት አላቸው ተብለው የተገመቱ ሰዎችን ለመለየትና ለማሰር ትኩረት የሚያደርጉባቸው ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ለአብነት ሙዚቀኞች፣ መምህራን፣ የተቃዋሚ አመራሮች እና ሌሎች ማህበረሰቡን ለቀጣይ አመጽ የማነሳሳት አቅም አላቸው ብለው የገመቷቸውን ሰዎችን ሰብስበው አስረዋል። በጸጥታ ሃይሎች ከታሰሩት እና ከታገደሉት በርካታዎቹ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች ናቸው፡፡ የፀጥታ ሃይሎች ያገቷቸውን ሰዎች ያሰቃያሉ አሊያም ያልተገባ አያያዝ ይፈጽሙባቸዋል፤ በርካታ የታገቱ ሴቶች የጸጥታ ሃይል አባላት በሆኑ ሰዎች መደፈራቸውን ገልጸዋል፡፡ የህግ ምክር አገልግሎት፣ በቂ ምግብ አሊያም በቤተሰብ የመጎብኘት እድል ያገኙት ታጋቾች እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ለዚህ ጥናት ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው በርካቶቹ በሚገኙበት ማህበረሰብ የተነሳውን አመጽ ለማፈን የተወሰደው እርምጃ መጠን እጅግ ከባድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከምዕራብ ወለጋ ዞን የ52 ዓመቱ ዩሴፍ እንደገለጸው “ሙሉ እድሜየን እዚህ ነው የኖርኩት፤ እንደዚህ አይነት ጭካኔ የተሞላበት አፈና አይቼ ግን አላውቅም፡፡ ተደጋጋሚና ያልተቆዋረጠ እስር እና ግድያ በህዝባችን ላይ ተፈጽሟል፣ እዚህ የሚገኝ ሁሉም ቤተሰብ ቢያንስ አንድ ልጅ ታስሮበታል፡፡ሁሉም ወጣቶች ታስረዋል፣ ገበሬዎቻቻችን ላይም ጥቃት እያደረሰባቸው ይገኛል አሊያም በእስር ላይ ናቸው፡፡”

የኢትዮጵያ መንግስት የተቃውሞ ሰልፍ አድራጊዎቹ በመንግስት እገዳ ከጣለባቸው ተቃዋሚ ቡድኖች ጋር ግንኙነት አላቸው ብሏል፤ ይህ ደግሞ ህዝባዊ ጥያቄን ለማቃለል የተለመደ የመንግስት ታክቲክ ነው፤ እንዲሁም በርካታ የተቃዋሚ አባላትን በሃገሪቱ አፋኝ በሆነው የፀረ ሽብር ህግ መሰረት ክስ መስርቶባቸዋል፡፡ በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ አክብሮት ያለው የተቃዋሚ መሪ አቶ በቀለ ገርባ ከ23ቱ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ ፓርቲ (ኦፌኮ) ከፍተኛ አመራሮች ጋር ለወራት ያህል በእገታ ላይ ከቆዩ በኋላ በጸረ-ሽብር ህጉ መሰረት ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡ ፓርቲው በህግ የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ ነው፡፡ አቶ በቀለ ለአመጽ አልባ እንቅስቃሴ እና በኢትዮጵያ በተካሄደው እና በተጭበረበረው የምርጫ ሂደት ላይ ኦፌኮ ላደረገው ዘላቂ ተሳትፎ ዉስጥ ወሳኝ ምና የተጫወተ ሰው ነው። በአዲስ አበባ በሚገኘው የዩናይትድ ስቴትስ (አሜሪካ) ኢምባሲ ፊት ለፊት ሰላማዊ ሰልፍ ያደረኩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪችም በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ደንብ ተከሰዋል፡፡

የጸጥታ ሃይሎች በትምህር ቤቶች ቅጥር ግቢ ውስጥ እና በአካባቢው ስለሚኙ እንዲሁም መምራን እና ተማሪዎች በመታሰራቸው አሊያም ተማሪዎች ወደ ትምህት ቤት ለመሄድ በመፍራታቸው ምክንያት ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ባሉ የትምህርት ተቋማት የትምህርት አገልግሎት ተስተጓጉሏል፡፡ በአንድ አንድ አካባቢዎች የመንግስት ባለስልጣን አካላት ተቃውሞን ለመግታት በሚል ለሳምንታት ያህል ትምህር ቤቶችን በግዜያዊት እንዲዘጉ አድርገዋል፡፡

የአሁኑ የጸጥታ ሀይሎች ጭቃኔ የተሞላበት ምላሽ በኦሮሚያ ውስጥ ከረዥም ግዜ ጀምሮ ያመኑበትን ሃሰብ በነጻነት የሚገልጹ ሰዎች ላይ በተከታታይ ከሚፈፀምመው ጥቃቶች የቅርቡ እንጅ የመጀመሪያ አይደለም። እ.አ.አ. ከሚያዚያ እስከ ሰኔ 2014 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በምዕራብ ኦሮሚያ ማስተር ፕላኑ ላይ የተቃውሞ ሰልፍ ሲያደርጉ የጸጥታ ሃይሎች ከመጠን ያለፈ ሃይል በመጠቀማቸው በደርዘኖች የሚቆጠሩትን ገድለዋል፡፡ እ.አ.አ. በ2014 ዓ.ም በመንግስት የጸጥታ ሀይሎች የተገደሉትን እና በዘፈቀደ የታሰሩትን ሰዎች በተመለከተ መንግስት የሚመረምር ገለልተኛ አካል እንዲኖር አልደገፈም፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የመገናኛ ብዙሐን ነጻነትን ለመገደብ የሚያደርገውን ጥረት በመጨመር ቀድሞውንም ቢሆን በኢትዮጵያ የከፋ ሁኔታ ዉስጥ የሚንቀሳቀሱትን ምድያዎች አፍነዋል። በመሆኑም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የመረጃ ማግኘ መንገዶችን ዘግቷል፡፡ ፌስቡክን ጨምሮ ሌሎች የማህበራዊ ድረ-ገጾች መረጃን ለማሰራጨት ቁልፍ ሚና እየተጫወቱ ስለነበረ እ.አ.አ. በመጋቢት ወር ጀምሮ መንግስት የማኅበራዊ ድረ-ገጾችን ማገድ ጀመረ፡፡ ለአብነት ያህል መሰረቱን አሜሪካ ያደረገውን ኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክን (ኦኤምኤን)ጨምሮ በዲያስፖራ የሚተዳደሩ የቴሊቪዥን ጣቢያዎችን የገደበ ሲሆን ፣ ግለሳብ ቤቶች ላይ እና ንግድ ቦታ ያሉ የግል ሳተላይት ዲሾችን ነቃቅሏል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በዘፈቀደ ይዞ ያገታቸውን ሁሉንም ታጋቾች መፍታት እና ክሶቹን ማንሳት አለበት፡፡ እንዲሁም የጸጥታ ሃይሎች ያልተመጣጠነ ሃይል ስለመጠቀማቸው ተዓማኒነት ያለው፣ ገለልተኛ እና ግልጽ ምርመራ እንዲካሄድ መደገፍ አለበት፡ ፡ ተጠያቂዎቹን በተገቢው መልኩ መቅጣት ወይንም መክሰስ ይገባዋል፡፡ በተጨማርም የጥቃቱ ሰለባ ለሆኑት ተገቢው ካሳ ሊከፈላቸው ይገባል፡፡ እነዚህን እርምጃዎች መውሰድ በኢትዮጵያ መንግስት እና በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ መተማመን እንደገና ለመፍጠር መሰረታዊ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ጭካኔ የተሞላበት አፈና ከዓለማቀፉ ማህበረሰብ  በጣም ጠንካራ እና የተባበረ ምላሽ ያሻል። የአውሮፓ ህብረት አፈናውን በማውገዝ ጠንካራ አቋም ያሳለፈ ሲሆን ሌላ አቋም ደግሞ ከዩናይትድ ስቴትስ (አሜሪካ) ሴኔት ተላልፏል፤ ከእነዚህ በስተቀር ሌሎች የአለም አቀፍ መህበረሰቦች በኦሮሚያ ለሚደረገው አፈና ላይ ከባድ ጸጥታን መርጠዋል። የኢትዮጵያ አፋኝ አስተዳደር የሃገሪቱን  የረዥም ጊዜ መረጋጋት እና ምጣኔ ሃብታዊ እድገት እጅግ ከፍተኛ ስጋት ዉስጥ ጥሏል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ተዓማኒነት በለው እና በገለልተኛ ቡድን ምርመራ እንዲካሄድ እንዲደግፍ የተሳበሰበ የዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ ግፊት ወሳኝ ነው፡፡ የብሄራዊ ደረጃ የማጣራት ሂደቱ ሙሉ በሙሉ የመንግስት ገለልተኛ የመሆን እድሉ ዝቅተኛ በመሆኑ ዓለምዓቀፍ ተሳትፎ እንዲኖረው ጥያቄ መቅረብ አለበት፡፡ በመጨረሻም የኢትዮጵያ ዓለምዓቀፍ የልማት አጋሮች በኦሮሚያ ለሚገኘው የልማት መርሐግብራቸው የሚሰጡት እርዳታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አሊያም በግዴለሽነት የሃገሪቱን እንዲሁም የዓለምዓቀፍ ህግን በሚጥስ መልኩ ህዝቦችን በሃይል የማፈናቀል ድርጊት ስላለማመቻቸቱ ማጤን ይገባቸዋል፡፡

# የማሻሻያ ሃሳብ

## ለኢትዮጵያ መንግስት

ተቃዎሞ ሰልፈኞች ላይ ከተገቢው በላይ ሃይል መጠቀምን በተመለከተ

- የጸጥታ ሃይሎች ከተገቢው መጠን በላይ ሃይል ስለመጠቀማቸው በተመለከተ ተዓማኒነት ያለው፣ ገለልለተኛ እና ግልጽ ምርመራ እንዲካሄድ ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡ ምርመራው የተገደሉትን እና ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን ስም ዝርዝር ሙሉ በሙሉ መመዝገብ እና ማካተት አለበት፡፡ የሞት ወይንም የአካል ጉዳት በደረሰበት ሁሉ ድርግቱ የተከሰተበትን ሁኔታ እንዲሁም የመንግስት የፀጥታ ሃይሎች ያደረሱትን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እስከ ምን ደረጃ እንደነበር ማካተት ይኖርበታል፡፡
- በተቃውሞ አድራጊዎቹ ላይ ያልተመጣጠነ የሃይል ርምጃ የወሰዱ ሁሉም የጸጥታ ሃይሎች ያለምንም የማዕረግም ሆነ የደረጃ ልዩነት ሊቀጡ ወይንም ተገቢው ክስ ሊመሰረትባቸው ይገባል፡፡
- የተባበሩት መንግስታት የህግ አስከባሪ ባለስልጣን አካላት ስለ ሃይል እና የጦር መሳሪያ አጠቃቀም በተመለከተ ካስቀመጠው መሰረታዊ መርህ ጋር በሚጣጣም መልኩ የህግ አስከባሪ እና የጸጥታ ጥበቃ አካላት ለአባላቶቻቸው ማንኛውንም አይነት ሃይል መጠቀም የሚቻለው እውነተኛ እና ወዲያው ሊደርስ የሚችል አደጋ ሲኖር ብቻ መሆኑን እንዲሁም ከተገቢው መጠን ያለፈ ሃይል መጠቀም እንዲሚያስቀጣ ግልጽ ትዕዛዝ መውጣት አለበት፡፡ በጦር መሳሪያን መጠቀም የሚቻለው ህይወትን ለመታደግ ብቻ እና አደጋውን በሌላ መንገድ ማስቀረት የማይቻል ሲሆን ብቻ መሆኑ መገለጽ አለበት፡፡ የጦር መሳሪያ የሚይዙ ባለስልጣናት መሳሪያ መያዝ ሊፈቀድላቸው የሚገባው የመሳሪያውን አጠቃቀም በተመለከተ የሚሰጠውን ልዩ ስልጠና ከወሰዱ በኋላ መሆን አለበት፡፡ የህግ አስከባሪ አካላት አማራጭ የሃይል መሳሪያ አጠቃቀም በተመለከተ ልዩ ስልጣና ሊሰጣቸው የሚገባቸው ሲሆን ይሄውም የጦር መሳሪያ የመጠቀም እድላቸውን ለመቀነስ ባለመ መልኩ የተቀረፀ መሆን አለበት፡፡

ዘፈቀዳዊ እገታን በተመለከተ

- በእስር ላይ የሚገኙ እና ክስ ያልተመሰረተባቸው አሊያም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሃሳብን የመግለጽ፣ የመደራጀት እና የመሰብሰብ ነጻነቶችን የመሳሰሉ መሰረታዊ መብቶቻቸውን ስለተገበሩ ክስ የተመሰረተባቸው ሰዎች በአስቸኳይ ይፈቱ፡፡
- ሰላማዊ ሰዎችን በወታደራዊ ካምፖች እና ማጎሪያ ቦታዎች ማገት ይቁም እንዲሁም ሁሉም ግለሰቦች በይፋ በሚታወቁ የእስር ቤቶች መታሰር እንዳለባቸው ማረጋገጥ አለበት፡፡

አስገድዶ ሰዎችን የመሰወር ተግባርን በተመለከተ

- የታገቱ ሰዎች ስም፣ ያሉበትን ቦታ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ለሁሉም የታገቱ ግለሰቦች ቤተሰቦች በአስቸኳይ መነገር አለበት፡፡
- ቤተሰቦች ስለጠፉ ወይንም ተገደው ስለመሰወራቸው ስለሚያምኑ ሰዎች በተመለከተ ጥያቄ በያቀርቡበት ጊዜ ሁሉም ባለስልጣን አካላት ፈጣን ምላሽ መስጠት አለባቸው፤ ሰዎቹ የት እንደሚገኙ እና የሚቀጥለው እጣ ፋንታቸው ምን እንደሚሆን የሚታወቀውን ሁሉንም መረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡ እንዲሁም መረጃ ባልተገኘበት አጋጣሚ የሚያስፈልገውን መረጃ ለማግኘት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡
- ሁሉም ተገደው እንዲሰወሩ የተደረጉ ሰዎች በአስቸኳይ መፈታት አለባቸው አሊያም በዳኛ ፊት ቀርበው በህግ ሊታወቅ የሚችል ጥፋት ስለማጥፋታቸው ክስ ሊቀርብባቸው ይገባል፡፡
- ሁሉንም ግለሰብ ተገዶ ከመሰወር ለመጠበቅ የወጣውን ዓለምዓቀፍ ስምምነት የሃገሪቱ የህግ አካል እንዲሆን መፅደቅ አለበት፡፡

የእስር አያያዝን በተመለከተ

- ሁሉም እስረኞች የእስረኞች አያያዝን በተመለከተ ተከልሶ በቀረበው የእስረኞች አያያዝ ቢያንስ ቢያንስ ዝቅተኛ የአለም አቀፍ መስፈርትን (የማንዴላ ህጎች በመባል የሚታወቀው) ያሟላ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡
- በአፋጣኝ፣ በግልፅኝነት እና በገለልተኛነት እስረኞች ላይ በእስርቤቶች ስለመፈጸሙ የማሰቃየት ተግባር የቀረቡ ክሶች መመርመር አለበቸው።፤ እንዲሁም ጥቃት የፈፀሙ ሁሉም ግለሰቦች ያለምንም የማዕረግ እና የደረጃ ልዩነት ሊቀጡ ወይንም ክስ ሊመሰረትባቸው ይገባል፡፡
- በግድ የእምነት-የክህደት ቃል ማስጠት፣ ክልከላ ለተጣለባቸው ቡድኖች ድጋፍ ስለማድረጋቸው የተወነጀሉ እስረኞችን መበቀል እንዲሁም ሌሎች ቅጣቶችን ጨምሮ በእስር ቤቶች ያልተገባ አያያዝ ማድረግ በምንም መልኩ አሳማኝ ምክንያት ሊኖረው እንደማይችል ግልጽ በማድረግ በይፋ እና በግልጽ በእስረ ቤቶች የሚፈጸም የማሰቃየት ተግባር እና ሌላ አይነት ያልተገባ አያያዝን ማውገዝ አለበት፡፡
- በህግ ቁጥጥር ስር ያሉ ሁሉም ግለሰቦች የህግ ጠበቃ የማግኘት መብትን፣ በቃል መቀበያ ጊዜ ሁሉንም የህግ ምክር አገልግሎቶች ማቅረብ፣ እንዲሁም በቤተሰብ የመጎብኘት እና የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብቶችን ጨምሮ መሰጠት ያለባቸውን ህጋዊ ከለላዎች በላቀ ሁኔታ ማሻሻል አለበት፡፡ ዓለም ዓቀፍ መስፈርትን የማያሟሉ ሁሉም እስር ቤቶች መዘጋት አለባቸው፡፡
- ዓለም ዓቀፍ የሰበዓዊ መብቶችን መስፈርት በተከተለ መልኩ ቃል የመቀበል ተግባርን በተመለከተ ለፌዴራል ፖሊስ፣ ለሰራዊቱ፣ ለክልላዊ ፖሊስ፣ ለአቃቢ ህግ እና ለሌሎች የህግ አስከባሪ አካላት ስልጠና መሰጠት አለበት፡፡
- በአስር ቤት ዉስጥ ምንም አይነት ግንኙነት እንዳይኖር አድርጎ ማሰር እና ለተራዘመ ጊዜ አንድን ግለሰብ ለብቻ አንድ ክፍል ውስጥ አስሮ የማስቀመጥ ተግባራት እንዲቆሙ አስፈላጊው እርምጃ ሁሉ መወሰድ አለበት፡፡
- ለዓለም-ዓቀፍ የተራድኦ እና የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እና ለዲፕሎማቶች ገደብ የለሽ ክትትል እንድያደርጉ እና ከሁሉም እስረኞች ጋር በግል ግንኙነት ለማድረግ እንዲችሉ በመፍቀድ፣ እስር ቤቶችን ክፍት በማድረግ በሁሉም የማገቻ ቦታዎች እና እስርቤቶች ገለልተኛ ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡
- የማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት እንዲሁም ኢሰብዓዊ ወይንም ሰብዓዊ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይንም ቅጣትን የሚቃወመውን አማራጭ የአለም አቀፍ የስምምነት ፕሮቶኮልን የሃገሪቱ የህግ አካል እንዲሆን መፅደቅ አለበት፡፡

ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በተመለከተ

- የሃገር ውስጥ እና የውጭ ሃገር ጋዜጠኞች በመላ ኢትዮጵያ የመንቀሳቀስ ነፃነታቸውን ለመገደብ የተጣለው እገዳ መነሳት አለበት፡፡ ይህም ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንደተፈጸመባቸው የተገለጹ ቦታዎች ድረስ የመንቀሳቀስ መብታቸውን ይጨምራል፡፡ የመገናኛ ብዙሃንን የመንቀሳቀስ መብት እንዲፈቅዱ ለፖሊስ እና የጸጥታ ሃይሎች መመሪያ መተላለፍ አለበት፡፡
- የማህበራዊ ድረ-ገጾችን፣ እና የፖለቲካ ፓረቲ ድረ-ገጾችን እና ጦማሪያንን ማገድ መቆም አለበት፤ እንዲሁም ወደፊት እንደዚህ አይነት ድረ-ጾችን ላለማፈን በይፋ-ቃል መግባት አለበት፡፡
- የሬድዮ እና ቴሌቪዥን ጣቢያ ሞገዶችን የማፈን ተግባር ማቆም እና የሬድዮ እና ቴሌቪዥን ሞገዶችን ላለማፈን መትጋት አለበት፡፡

የልማት መርሐ-ግብር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥቃቶችን በተመለከተ

- በልማት መርሐ-ግብሮች ምክንያት ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችሉ ማሕበረሰቦች ጋር ክፍት እና ግልጽ ምክክር መደረግ አለበት፤ በተለይ ደግሞ በአዲስ አበባው የተቀናጀ የልማት ማሰተር ፕላን መሰረት ከመሬት የማፈናቀል አደጋ ያላቸው መርሃግብሮች ትኩረት ያስፈልጋቸዋል፡፡

- ከመሬታቸው የተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ብቻል ወደ መሬታቸው ተመልሰው እንድሰፍሩ፣ ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ቀድሞ ከነበራቸው አሊያም ይዘውት ወይንም ይጠቀሙበት ከነበረው አንጻር ተመጣጣኝ እና ተገቢው ካሳ ሊሰጣቸው፡፡

## ለኢዮጵያ ህግ ተርጓሚ አካል

- በማሰቃየት እና በሌላ ያልተገባ አያያዝ መንገድ የተገኙ ንግግሮች፣ የእምነት-የክህደት ቃሎች እና ሌሎች መረጃዎች በህግ ፊት ማስረጃ ሆነው ሊቀርቡ እንደማይገባ መረጋገጥ አለበት፡፡ ማስረጃዎች የተገኙት ሃይል በመጠቀም መሆኑ በተገለጸ ጊዜ የቀረበውን ቅሬታ ለመገምገም ባለስልጣን አካላቱ ማስረጃውን ያገኙበትን ሁኔታ ለፍርድ ቤት መረጃ እንዲያቀርቡ መጠየቅ አለባቸው፡፡
- የማሰቃየት እና ያልተገባ የእስር አያያዝ መፈጸሙ ከተገለጸ በአግባቡ የቀረበው ቅሬታ መመርመር አለበት እንዲሁም ያልተገባ አያያዝ እንደተፈጸመባቸው ቅሬታውን ያቀረቡ እስረኞች ድርግቱን በመናገራቸው ማረሚያ ስመለሱ የበቀል ርምጃ እንዳይፈጸምባቸው ሊጠበቁ ይገባል፡፡

## ለተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ምክር-ቤት

- ኢትዮጵያ በተቃውሞ ሰልፈኞች ላይ ከተገቢው መጠን ያለፈ ሃይል መጠቀም እንድታቆም እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እንዳትፈጽም ጫና መደረግ አለበት፡፡ ተቃዎሞዎቹ ላይ ለተፈፀሙትን ግድያዎች እና ሌሎች ጥቃቶች ሃላፊነት ያለባቸውን ሰዎች በመያዝ ተጠያቂ እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡
- በተቃውሞው ወቅት ተይዘው የታሰሩ እና በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ እና በጸረ-ሽብር ህጉ መሰረት ክስ የተመሰረተባቸው ሁሉም ሰለማዊ ሰልፈኞች፣ የተቃዋሚ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች እና ሌሎች በዘፈቀደ የታሰሩ ሰዎች እንዲፈቱ ጫና መደረግ አለበት፡፡
- ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ልዩ ብድን ወደሃገሯ እንድታጋብዝ ልትጠየቅ ይገባል፡፡ ይሄም ማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት ኢ-ሰብዓዊ ወይንም ክብርን አዋራጅ አያያዝ አሊያም ቅጣትን በተመለከተ ቁጥጥር የሚያደረገውን የተባበሩት መንግስታት ልዩ ራፖርተር፣ ሰላማዊ የመደራጀት እና የመሰብሰብ ነጻነት መብቶችን የሚመለከተው የተባበሩት መንግስታት ልዩ ራፖርተር እንዲሁም ዘፈቀዳዊ እስርን የሚመለከተው የስራ ብድን ኢትዮጵያን መጎብኘት አለባቸው፡፡
- የፀጥታ ኃይሎች የተጠቀሙትን ከመጠን ያለፈ ሃይል በተመከለከተ ተዓማኒነት ያለው፣ ገለልተኛ እና ግልጽ ምርመራ እንዲደረግ ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡ ምርመራው የተገደሉትን እና ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ስም ዝርዝርን ሙሉ በሙሉ መመዝገብን ማካተት አለበት፣ የሞት ወይንም የአካል ጉዳት ያደረሰው እያንዳንዱ አደጋ የነበረበትን ሁኔታ እንዲሁም የመንግስት የፀጥታ ሃይሎች ያደረሱትን የሰብዓዊ መብት ጥሰት መጠን መካተት ይኖርበታል፡፡

## ለኢትዮጵያ ዓለምዓቀፍ አጋሮች

- ኢትዮጵያ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ከተገቢው መጠን ያለፈ ሃይል መጠቀም በአፋጣኝ እንድታቆም እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እንዳትፈጽም ጫና መደረግ አለበት፡፡ የኦሮሞ ተቃዎሞዎች ጋር በተያያዘ ለተፈፀሙት ግድያዎች እና ሌሎች ጥቃቶች ሃላፊነት ያለባቸውን ሰዎች በመያዝ ተጠያቂ እንዲሆኑ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ወዳጆችና ሌሎች የሚያሳስባቸው መንግስታት ጫና ማድረግ አለባቸው፡፡
- የፀጥታ ኃይሎች የተጠቀሙትን ከመጠን ያለፈ ሃይል በተመከለከተ ተዓማኒነት ያለው፣ ገለልተኛ እና ግልጽ ምርመራ እንዲደረግ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡ ምርመራው የተገደሉትን እና ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ሙሉ በሙሉ መመዝገብን ማካተት አለበት፣ የሞት ወይንም የአካል ጉዳት ያደረሰው እያንዳንዱ አደጋ የነበረበትን ሁኔታ እንዲሁም የመንግስት የፀጥታ ሃይሎች ያደረሱትን የሰብዓዊ መብት ጥሰት መጠን በተመለከተ መካተት ይኖርበታል፡፡

- በተቃውሞው ወቅት ተይዘው የታሰሩ እና በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ እና በጸረ-ሽብር ህጉ መሰረት ክስ የተመሰረተባቸው ሁሉም ተቃውሞ አድራጊዎች፣ የተቃዋሚ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች እና ሌሎች በዘፈቀደ የታሰሩ ሰዎች እንዲፈቱ በይፋ ጥሪ ማቅረብ እና በግል ጫና ማድረግ አለባቸው፡፡
- ከፌዴራል ፖሊስ፣ ክልላዊ ፖሊስ እና ብሄራዊ ሰራዊቱ ጋር ተያያዥነት ላለው መርሐ-ግብር የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ ለጋሾች በህዝባዊ ተቃውሞው ወቅት እና በእስር ቤቶች ውስጥ በጸጥታ ሃይሎች ስለመድረሱ የተነገረውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት በተመለከተ ምርመራ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህም ለጋሾች የሚሰጡት የገንዘብ ድጋፍ ለሰብዓዊ መብት ጥሰት  አስተዋጽኦ ስላለማበረከቱ መረጋገጥ አለበት፡፡
- የፍርድ ሂደቶች ዓለምዓቀፍ መስፈርትን ያሟሉ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የተቃውሞ አድራጊዎችን እና ሌሎች መሰረታዊ መብቶቻቸውን በመጠቀማቸው ብቻ የታሰሩትን ሰዎች የፍርድ ሂደት በተመለከተ የሚደረገው ክትትል መጨመር እና መጠናከር አለበት፡፡
- በይፋ እና በግል በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት በእስር ቤቶች ስለሚፈጸሙ እስረኞችን ማሰቃየት፣ ያልተገባ አያያዝ እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንደሚያሳስባቸው መግለጽ አለባቸው፡፡
- በዘፈቀደ የታሰሩ ተቃውሞ አድራጊዎች፣ የተቃዋሚ ፖለቲከኞች እና ጋዜጠኞች የእስር አያያዝ ሁኔታን ለመከታተል የዓለምዓቀፍ ተራድኦ ድርጅቶች፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና ዲፕሎማቶች እስር ቤቶችን ያለገደብ እንዲጎበኙ መጠየቅ አለባቸው፡፡
- የመሰብሰብ እና ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት መብቶች መገደብ የሀገሪቱን ዘለቄታዊ ልማት እና ደህንነት ላይ የሚደቅነው አደጋ እንደሚያሳስባቸው በይፋ እና በግል ሉሁም የመንግስት ባለስልጣናት መገለጽ አለበት፡፡
- መንግስት የደረሰውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ካልመረመረ እና ተመሳሳይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወደፊት እንደማይፈጸም ካላረጋገጠ በስተቀር ሰዎችን የማፈናቀል አደጋ እንዳለው ከታወቀው አዲስ አበባ ዙርያ ለሚደረግ ምንም አይነት የመንግስት የልማት መርሐ-ግብር ላይ በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ፣ የዲፕሎማሲ ወይንም የቴክኒካል ድጋፍ መሰጠት የለበትም፡፡
- ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ልዩ ብድን ወደ ሃገሯ እንድትጋብዝ ልትጠየቅ ይገባል፡፡ ይሄም የማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት ኢ-ሰብዓዊ ወይንም ክብር አዋራጅ አያያዝ አሊያም ቅጣትን በተመለከተ ቁጥጥር የሚያደረገው የተባበሩት መንግስታት ልዩ ራፖርተር፣ ሰላማዊ የመደራጀት እና የመሰብሰብ ነጻነት መብቶችን የሚመለከተው የተባበሩት መንግስታት ልዩ ራፖርተር እንዲሁም ዘፈቀዳዊ እስርን የሚመለከተው የስራ ብድን ኢትዮጵያን መጎብኘት አለባቸው፡፡

## ለኬንያ፣ ሱዳን፣ ግብጽ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሌላንድ፣ እና ሶማሊያ ለሚገኙ ባለስልጣናት

- በኢትዮጵያ መንግስት ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ ሸሽተው ወደ ሀገራችሁ የተሰደዱ እና የጥገኝነት ጥያቄ ያቀረቡ በተለይ የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች ጉዳይ በአፋጣኝ እና በተገቢው ሊስተናገዱ እንዲሁም ያቀረቡት ማመልከቻ በአፋጣኝ ሊታይላቸው እና ሊደርስባቸው ከሚችል ጥቃት ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

## ለባለሃብቶች

የልማት ስራ ሊያከናውኑ የሚችሉ ባለሃብቶች የሚከተሉትን ጉዳዮች ማጤን ይገባቸዋል፤

- የታቀደው ልማት ሰዎችን ከመሬታቸው የሚያፈናቅል ስሆን የአካባቢው ማህበረሰብ አባላት፣ ገበሬዎች፣ አርብቶ አደሮች ጋር በቂ ምክክር ስለመደረጉ እና ከመሬቱ ለሚፈናቀል ወይንም በተለምዶ ሲጠቀሙበት ለኖሩት አካላት የኢትዮጵያ ህግ በሚፈቅደው መሰረት መንግስት ተገቢውን ካሳ ስለመክፈሉ፣
- የአካባቢያዊ የተፈጥሮ ጉዳት ጥናት ስለመካናወኑ እና ሊደርስ የሚችለው አካባቢያዊ የተፈጥሮ ጉዳት እንዲሁም ይኼንን ጉዳት ለመቀነስ የተነደፈውን ዘዴ በተመለከተ ለተጠቂው መህበረሰብ በይፋ መገለጽ አለበት። እነዚህ የአካባቢያዊ የተፈጥሮ ጉዳቶች ጥናት ዉጤት ለህዝብ እና ለተጎጂዎቹ ማህበረሰቦች በይፋ መገለጽ እና ማንም የሚያገኛቸው ቦታ መቀመጥ አለባቸው፡፡